DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS



ሚያዚያ (April) 9, 2018

ውድ የዲሲፒኤስ ቤተሰቦች፣

በዚህ በጋ (winter)፣ ትምህርት ቤቶች በበረዶ የተነሣ በመዘጋታቸው ምክንያት፣ የምጽፍልዎ ለዚህ ዓመት ወቅቱን የጠበቀ የትምህርት ቀናት መቁጠርያ ለማቅረብ ነው። በተጨማሪ በዚህ አጋጣሚ በጠቀም፣ በትምህርት ቤቶች የቀን መቁጠሪያዎች ለ 2018-2019 የትምህርት ዓመት እንዲጠቀሙባቸ ሀሳብ ለመስጠት ነው።

**የትምህርት ዓመት 2017-2018 የቀን መቁጠሪያ፣ የበረዶ ቀናት ለጦች**

ዲሲፒኤስ፣ በዚህ ዓመት ሁለት የበረዶ ቀናት ነበሩት። በዚህ መሠረትም፣ የዓመቱን የትምህርት ጊዚያት በሁለት ቀናት ለማ ራዘም እንፈልጋለን። ይህም ማለት በትምህርት ቤት የቀናት መቁጠሪያው ላይ የሚከተሉት ለውጦች ይደረጋሉ።

- **ዕረቡ፣ ሰኔ (June) 13, 2018** ሙሉ የትምህርት ቀን ሆኖ ይውላል።
- **ሀሙስ፣ ሰኔ (June) 14, 2018** ሙሉ የትምህርት ቀን ሆኖ ይውላል።
- **ዐርብ፣ ሰኔ (June) 15, 2018** ግማሽ የትምህርት መስጫ ቀን ሆኖ የሚውል ሲሆን፣ ተማሪዎች በ 12:15 ፒኤም ላይ ከትምህርት ቤት ይለቀቃሉ። ይህ የዓመቱ የመጨረሻ የትምህርት መስጫ ቀን ነው። መምህራን፣ የትምህርት ውጤት መረጃዎችን ለማጠናቀር ከሰዓት በኋላ ይሠራሉ።

እያንዳንዱ ቀን፣ መጀመሪያ በተመደበው ዐይነት ያለምንም ለውጥ እንዲሠራ ይደረጋል። እነዚህ ለውጦች ለተራዘም የት ምህርት ዓመት (Extended-Year) አያገለግሉም።

**የትምህርት ዓመት 2018-2019 የቀን መቁጠሪያ**

የሚቀጥለው የትምህርት ዓመት የዲሲፒኤስ የቀን መቁጠሪያ፣ አሁን በኦን ላይን (online) ላይን ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ እርስ ዎም እንዲመለከቱት (reference) ተያይዞልዎታል። በኦን ላይን dcps.dc.gov/page/dcps-calendars. ላይ ባለ ቀለም ቅጅውን ማለትም ግልባጩን እባክዎን ይፈልጉ።

እንደ ዘንድሮው ዓመት፣ በ 2018-2019 የትምህርት ዓመት፣ ሞዴል ይኖራቸዋል። የተራዘመ ዓመት፣ ሁለት ሣምንት ተጨ ማሪ ትምህርት ይኖራቸዋል። ለማስታውስ ያህል (13) ቱ የተራዘመ የትምህርት ዓመት ያላቸው ትምህርት ቤቶች ቀጥለው የተመለከቱት ናቸው።

- Garfield አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 8)
- H.D. Cooke አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 1)
- Hart መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 8)
- Hendley አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 8)
- Johnson መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 8)
- Kelly Miller መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 7)
- King አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 8)
- Luke C. Moore ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 5)
- Randle Highlands አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 7)
- Raymond Education Campus (ቀጠና 4)
- Roosevelt STAY ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 4)

- Thomas አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 7)
- Turner አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቀጠና 8)

<u>ለተለምዶው ትምህርት ቤቶች ጠቃሚ የቀን መቁጠሪያ ቀናት</u>

| | |
|---|---|
| የመጀመሪያ የትምህርት ቀን* | ነሀሴ (August) 20, 2018 |
| የበጋ ዕረፍት | ታኅሣሥ (December) 24, 2018 – ጥር (January) 1, 2019 |
| የካቲት (February) ዕረፍት | የካቲት (February) 18-22, 2019 |
| የጸደይ ዕረፍት | ሚያዚያ (April) 15-19, 2019 |
| የመጨረሻ የትምህርት ቀን** | ሰኔ (June) 14, 2019 |

<u>ለተራዘመ ዓመት የትምህርት ቤቶች የቀን መቁጠሪያ</u>

| | |
|---|---|
| የመጀመሪያ የትምህርት ቀን* | ነሀሴ (August) 13, 2018 |
| የበጋ ዕረፍት | ታኅሣሥ (December) 24, 2018 – ጥር (January) 1, 2019 |
| የካቲት (February) ዕረፍት | የካቲት (February) 18-22, 2019 |
| የጸደይ ዕረፍት | ሚያዚያ (April) 15-19, 2019 |
| የመጨረሻ የትምህርት ቀን | ሰኔ (June) 21, 2019 |

** አብዛኛዎቹ የቅድመ መዋዕለ ሕጻናት (Pre-K) ተማሪዎች (Pre-K3 እና Pre-K4) ሀሙስ ነሀሴ (August) 23 በመደበኛ የቀን መቁጠሪያ ትምህርት ቤት ትምህርት እና ነሀሴ (August) 16 ደግሞ ለተራዘም የትምህርት ዓመት ቀን አቆጣጠር፣ ትምህርት ቤቶች ትምህርት ይጀምራሉ። ሆኖም ይህ እንደ ትምህርት ቤቱ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል። ስለ ልጅዎ ትምህርት መጀመሪያ ቀን እርግጠኛ ካልሆኑ የልጅዎን ትምህርት ቤት ርእሠ መምህር ያነጋግሩ።*
*** ድንገት በረዶ የሚጥልበት ቀን ሆኖ ከተገኘ የመጨረሻው የትምህርት ቀን እንዲራዘም ይደረጋል።*

*ስለ 2018-2019 የትምህርት ዓመት ቀን መቁጠሪያ ቀናት ያላቸውን አስተያይቶች ጊዜ ወስደው ለሰነዘሩ በርካታ ቤተሰቦቻችንን አመሰግናለሁ። ይህን የትምህርት ዓመት በጠንካራ ሁኔታ ለማገባደድ እና በነሀሴ (August) ሌላ ስኬታማ የትምህርት ዓመት ለመጀመር በጉጉት እንጠባበቃለን!*

*ከልባዊ ሠላምታጋር፣*

*Wanda H. Legrand, Ed.D*
*Deputy Chancellor of Social, Emotional, and Academic Development*
*(የማኅበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የአካዳሚክ መዳበር ምክትል ቻንስለር)*